ዜናዎች

## ዶ/ር ተረፈ ወ/ጻድቅ በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድሏል

በነሐሴ ወር 1969 መኢሶን የትግል ስልት ለውጥ ማድረጉን እንዳስታወቀ ይታወሳል:: በዚህም አማካኝነት አንዳንድ አባሎቹን ወደ ህቡዕ የትግል መስክ አዛውሮ ነበር::

ዶ/ር ተረፈ ወ/ጻድቅና ከዚህ በታች ስማቸው የተዘረዘረው በሁለት ከሃዲያችና አንድ ተባባሪ አማካኝነት የነበረበት ቦታ ከተጠቆመ በኋላ በታህሳስ 30.1970 የመንግስት ወታደሮች በቦታው ደርሰው እጃቸውን እንዲሰጡ ካደረጉ በኋላ በቦታው ተረሸነዋል:

የተገደሉት

1. ዶ/ር ተረፈ ወ/ጻድቅ የትምህርት ሚኒስቴር
2. ባለቤቱ አጥናፍ
3. ከበደ ደሪባ የሸዋ ክ/ሀገር የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊ/ጽ/ቤት ሃላፊ
4. ኢዩብ ታደሰ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለደረባ የነበረ
5. መርዕድ ከበደ የአዲስ አበባና የአካባቢው የሕዝብ ድርጅት ጊ/ጽ/ቤት ባለደረባ የነበረ
6. ለማ ፊዳ ካድሬ ሸዋ ሕ.ድ.ጉዳይ ጊ.ጽ.ቤት
7. ሽመልስ አሳና ከፋ ክፍለ ሃገር የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊ.ጽ.ቤት ም/ ሃላፊ
8. ታደሰ የሸዋ ሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊ.ጽ.ቤት ሾፌር
9. አሰፋ ነምራ
10. ሁለት በጅባትና ሜጫ አውራጃ የነበሩ ካድሬያች

ስለእነዚህ ታጋዮችና ሌሎችም ባለፉት ወራት ስለወደቁት የመኢሶን አባሎችና ደጋፊዎች ዝርዝር ሐተታ ወደፊት እናወጣለን::

በተረፈ ግን በየቦታው የ"ፈርጣጩ" መኢሶን አባሎች ደጋፊዎች ናቸው ተብለው በሚጠረጠሩ ታጋዮች ላይ ክትትልና ማሳደድ አሁንም እንደቀጠለ ነው:: የስውርና የግለፅ የጥቃና እርምጃዎች መጠን እየጨመረ በመሄድ ላይ ይገኛል::